# ቅንጅት ካልጋሪ

Saturday, April 28, 2007

## የቅንጅት ሎጎ በወገኖቻችን ደም የታተመ የእወነት ማሕተም ነው!

የቅንጅት ሎጎ ለፍቅር፣ ለሰላም፣ ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለዜጎች መብት በአገራችን እውን መሆን በርግጠኝነት በተነሱ የህዝብ ልጆች ደም የታተመ የእወነት መህተም እንጂ የግለሰብ የንግድ ድርጅት አይደለም:: መሆንም አይችልም::

ዛሬ በእስር ያሉ ጀግኖች መሪዎቻችንና የነሱን ፈለግ የተከተሉ በርካታ ወገኖች ያላአንዳች ማመንታት ምትክ የሌለውን ህይወታቸውን የከፈሉለትን ቅንጅት እኛ ከሀገር ርቀን የምንገኝ ወገኖች የእምነታቸወ ዋስ ጠበቃ ሆነን የተለሙትን ትልም ዳር ለማድረስ በጋራ ተነሰተን ደፋ ቀና በምንልበት ወቅት የመርህ ደርጅታችንን አርማ እንደግል ንብረት አሰመዝግበው በዚህም ሳይገቱ እዳንገለገልበትም ሲነግሩን ሲያስነግሩን መስማት እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል::

በዚህ ምክንያት እኛ በካልገሪ የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ አባላት ይህንን አሳፋሪ የሆነ የክህደት ተግባር የሚፈጽሙ ጥቂት ግለሰቦችን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ እየመከርን እኛ ግን የቅንጅት ሎጎ የእምነት፣ የተስፋ አርማችን በመሆኑ ከመጠቀም የሚያግደን አንዳችም አካል እደማይኖር በአጽኖት እየገለጽን ሎጎውን በግል ሱቅ ስም ይዘናል ከሚሉ ግለሰቦችም ሆነ በማንኛውም መልኩ እንዳንጠቀም ለማገድ የሚሞክሩ ቢኖሩ የመከላከል ህጋዊ ብቃት ሊኖረን እንደምንችል ለመግለጽ እንገደዳለን::

በመጨረሻም በአለም ዙሪያ የሚገኝ የቅንጅት ደጋፊና አስተባባሪ አካላት እነዚህን የሕዝብ የእምነት ቃላ አጉዳዮችን በያሉበት እያሳፈረ በሀገር ቤት በሚደረገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ላይ ከምንግዜውም በላይ ሀይሉን አስተባበሮ እንዲነሳ ጥሪ እያቀረብን እኛ በካልጋሪ የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊዎች የሚጠበቅብንን ለማድረግ ዛሬም እንደትላንቱ በምንችለው ሁሉ ከቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ጎን በመቆም ሀገራዊ ግዴታችንን እንደምንወጣ በእርግጠኝነት መናገር እንፈልጋለን::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ቅንጅት ካልጋሪ